# የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት

## Catering and Tourism Training Institute

ቅጽ 1 ቁጥር 3 ነሐሴ 2011 ዓ.ም


## በቱሪዝም ትምህርት ክፍል ለመምህራን አቅም ግንባታ ስልጠና እየተሰጠ ነው





በህዝብና ዓለማቀፍ ግንኙነት የተዘጋጀ

ነሀሴ 30/2011 ዓ.ም

**ሆ.ቱ.ማ.ኢ ነሀሴ 15/2011ዓ.ም**

በሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በቱሪዝም ትምህርት ክፍል ለመምህራን አቅም ግንባታ ስልጠና እየተሰጠ መሆኑን የትምህርት ክፍል ኃላፊው አቶ ኪዳኔ ገረሱ ገለፁ:: ኢንስቲትዩቱ በየዓመቱ እንደሚያደርገው መጪውን የትምህርት ዘመን በአዲስ እና በተለያዩ የክህሎት ማዳበሪያ መስኮች የመምህራንን አቅም ለመገንባት እንዲያስችለው ለ16 መምህራን ስልጠና በመሰጠት ላይ ይገኛል::

ስልጠናውን የሚስጡት ከኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን በሙያው ከፍተኛ ልምድ ያላቸው አቶ ተከተል ፈጠነ ሲሆኑ በሶስት የስልጠና ዓይነቶች ማለትም በዱር እንስሳትና አእዋፋት ላይ ያተኮረ (Flora & Fauna)፣ Ornithology or bird-ing እንዲሁም Ethiopian painting & Art በእነዚህ ዘርፎች ከ14/12/2011 ዓ.ም እስከ ጳጉሜ 6/2011ዓ.ም ድረስ እንደሚቀጥል የተናገሩት የትምህርት ክፍሉ ኃላፊ ከክህሎት ስልጠናው በተጨማሪ የተግባር የመስክ ስልጠና ጉዞም እንደሚኖራቸው ገልጸዋል::

## የተቋሙ የበላይ አመራሮች በተገኙበት በ2012 በጀት ዓመት ዕቅድ ዙሪያ ምክክር ተደረገ

በሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ የሚገኙ የሥራ ክፍሎች፣ ኃላፊዎችና በበጀት ዓመቱ ዕቅዶች ዙሪያ ሰፊ ውይይት ተደረገ::

የ2012 በጀት ዓመት ዕቅድ ያቀረቡት የተቋሙ ዕቅድ ዝግጅትና ግምገማ ዳሬክተር አቶ ሀይሉ ነገዎ በበጀት ዓመቱ የስልጠና ጥራትና ተደራሽነትን ማሻሻል፣ የጥናትና ምርምር እና የምክር አገልግሎቶችን የማስፋት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙሪያ ሰፊ ስራዎችን መሰራት ስለተቋሙና ተቋሙ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች መረጃዎችን በሰፊው ተደራሽ ማድረግ እና ምቹ የሥራ አከባቢን መፍጠር በዋናነት የተያዙ ዕቅዶች መሆናቸውን ገልፀዋል:: አቶ ገዛኸኝ አባተ የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር በበኩላቸው የተቋሙ ዕቅድ ወቅታዊና የተያዘውን ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት መሆን እንዳለበት ተናግረዋል::

ሁሉም የሥራ ክፍል የራሱን ተግባርና ኃላፊነት መወጣት እንዳለበትም ገልጸዋል::

የኢንቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አሰቴር ዳዊት እንደገለጹት እነዚህ የታቀዱ ስራዎች ከዳር ለማድረስ ከሀገራዊ ዕቅድ አንጻር ታይቶ መዘጋጀቱ ዕቅዱን የተሻለ ያደርገዋል ::

ሁሉም ሰራተኞች ለዕቅዱ ስኬት አዳዲስ አሰራሮችን በመዘርጋት ርብርብ እንዲያደርጉ በማሳሰብ ምቹ የሥራ አከባቢን ለመፍጠር ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል:: በተጨማሪም የገነት ሆቴል የተቋሙ አካል በመሆኑ ሆቴሉ ያዘጋጃቸው ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የሁሉም ርብርብ እንደሚያስፈልግ ወ/ሮ አስቴር ተናግረዋል::







## የቱሪዝም መዳረሻዎችና ሆቴሎችን የመስክ ጉብኝት ሊያደርግ እንደሆነ ተገለጸ

**.ቱ.ሥ.ማ.ኢ ነሐሴ 10/2011 ዓ.ም** የሆቴልና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የቱሪዝም መዳረሻዎችና ሆቴሎች የአካል ምልከታ ለማድረግና ግብዓት ለማሰባሰብ የመስክ ጉብኝት ሊያደርግ እንደሆነ ተገለጸ።

ኢንስቲትዩቱ ላለፉት 50 ዓመታት የሆስፒታሊቲ ኢንዱሰትሪን መደገፍ የሚችል በስኩ የሰለጠነ የሰው ኃይል ሲያቀርብ የቆየ አንጋፋ ተቋም ሲሆን

**ሆ**የስልጠና ጥራትን ለማሻሻልና ከሆቴሎችና ከቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች ግብዓት ማሰባሰብ በዚህ የዝግጅት ምዕራፍ የታቀዱ ሥራዎች እንደሆኑ የጉዞው አስተባባሪና የቱሪዝም ትምህርት ክፍል አቶ ኪዳኔ ገረሱ ገልፀዋል።

በተጨማሪም ጉዞው የተቋማችንን ማህበረሰብ በማሳተፍ ክፍተቶችን ከመነሻቸው በመለየት በቀጣይ የስራ ዘመን ለሚሰሩ ስራዎች ለእቅድ ዝግጅት ግብአት ማሰባሰብ፣ የተቋሙን ዓላማና ራእይ ለማሳካት ከክልሎች በተለይ ከደቡብ ምስራቅ እና ምስራቅ የቱሪዝም መዳረሻዎች ላይ የነበረንን ትስስር በአካል በመገምገም በነበሩን የጋራ ስራዎች ላይ ያስመዘገብናቸውን ጠንካራ ተግባራት እና ውስንነቶቻችንን በመለየት በቀጣይ በአካባቢው የሥልጠና ትኩረትና የሰው ኃይል መሙላት እንደሚገባ ቅድመ ዳሰሳ ለመንደፍ ያስችላል።

በሌላም በኩል ይህን መሰል ጉዞ መዘጋጀቱ የተቋሙ ማህበረሰብ ከተሰማራበት ስራ አንፃር ከመዳረሻዎቹ (ከባለ ድርሻ አካላት) ጋር በመወያየት ለተቋማችን ስኬት ገንቢ ሀሳቦችን በመውሰድ የቀጣይ ትግበራዎችን ከመቼውም ጊዜ በተሻለ ስኬታማና የተሳለጠ የስራ እቅድ-ክንውን እንዲኖር የሚያግዝ መሆኑን አቶ ኪዳኔ ይገልፃሉ።

ጉዞው ከአዲስ አበባ፣ አሰላ ፣ ባሌ ሮቤ ፣መታሃራ ፣ ሀረር ፣ድሬደዋ ፣አዳማ ሲሆን በየከተሞቹ የሚገኙ ሆቴሎችና የቱሪዝም መዳረሻዎች ይጎበኛሉ።

የጉዞው መነሻም ቅዳሜ ነሐሴ 18 እንደሚሆን ተገልጿል።



*ሆ.ቱ.ማ.ኢ ነሀሴ 19/2011ዓ.ም*

### *የኢንስቲትዩቱ ሰራተኞችና አመራሮች ባሌ በሚገኙ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ላይ ገብኝት አደረጉ።*

የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሰራተኞች፣መምህራንና አመራሮች ባሌ ዞን በሚገኙ አንዳንድ ሆቴሎችና የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክን ጎበኙ። ጉብኝቱ ክፍተቶችን ከመነሻቸው በመለየት በቀጣይ የስራ ዘመን ለሚሰሩ ስራዎች ለእቅድ ዝግጅት ግብአት ማሰባሰብ መቻሉንና የስልጠና ጥራትን በማሻሻል በቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ የሚሰጡ የአገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል ለዕቅድ ዝግጅት መነሻ የሚሆኑ ግብቶች የተገኑበት መሆኑን የጉዞው አስተባባሪና የቱሪዝም ትምህርት ክፍል ኃላፊ አቶ ኪዳኔ ገረሱ ገልጸዋል።

የቱሪዝም መምህር ሰይድ የሱፍ እንዳሉት የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ከሌሎች የሀገራችን ፓርኮች በሀገራችን ብቻ የሚገኙ ብዙ አእዋፋትና እንሰሳት የሚገኙበት በመሆኑ ለፓርኩ የአካባቢው ማህበረሰብና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን እንክብካቤ እንዲያደርጉለት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ለሰሩ ይገባል ብለዋል።

በተጨማሪም የሚታዩ የአገልግሎት ጥራት ችግሮችን ለማስተካከል ለአስጎብኚዎችና በሆቴል ስራ ላይ ለተሰማሩ አካላት የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎችን በመስጠት አቅማቸውን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ የሀገራችን የቱሪዝም ሁኔታ በተለይም የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ሁልጊዜ የቱሪስት ፍሰት ያለበት በመሆኑ ይህን በብቃት ሊወጣ የሚችል የሰው ሀይልን ማፍራትና በቂ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ሆቴሎች እንዲኖሩ



ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ በዚህ በባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክና አንዳንድ ሆቴሎች ላይ በተደረገው ጉብኝት የተለዩ ችግሮች ለቀጣይ እቅድ እንደግብዓት የሚወሰዱ መሆኑን ጠቅሰው በተለይም የሰው ሀይል ብቃት ጋር የተያያዙ ክፍተቶችን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን ስልጠና እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡




የቱሉዲምቱ ተራራ



ሰራተኞች ስለ ቦታው ገለፃ ሲደረግላቸው

# የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ



ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ ነሀሴ 19/2011 ዓ.ም



የባሌ ተራሮች ብሄራዊ ፓርክ በ1962 ዓ.ም የተመሰረተው ሲሆን ከአ.አ. በ400 ኪ.ሜ ርቀት በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ይገኛል፡፡ ስፋቱ ወደ 2200 ኪ.ሜትር ስኩዌር የሚደርስ ከሰሜን ወደ ደቡብ 74 ኪ.ሜ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ ደግሞ 53 ኪ.ሜትር ይሰፋል፡፡ ፓርኩ ከባህር ወለል በላይ ከ1450 እስከ 4377 ጫማ ባለ ልዩነት ውስጥ የሚገኙ አካባቢዎችን ያካትታል፡፡ 4377 ጫማ የሚረዝመው እና ከኢትዮጵያ በከፍታው ሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የቱሉ ዲምቱ ተራራን ጨምሮ የአፍሮ አልፓይን ከፍተኛ ቦታዎች በዚህ ፓርክ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የባሌ ተራሮች ከፍተኛ አካባቢ በተለያዩ መንገድ የተፈጠሩ ሀይቆች እርጥበት አዘል መሬቶች፣ የእሳተ ጎሞራ ቅሪቶችን አቅፎ ይዟል፡፡

ፓርኩን ልዩ የሚያደርገው ሌላው ነገር በኢትዮጵያ ትልቁና ወደ ሰባት ሺህ ኪሎ ሜትር ስኩዌር የሚሸፍነው ‹‹የሐረና ደን›› በውስጡ በመገኘቱ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ከ1600 በላይ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ዓይነት ዕፅዋቶች፣ 78 ዓይነት አጥቢ የዱር እንስሳትና ወደ 200 የሚጠጉ አእዋፋት በፓርኩ ተጠልለው ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም መካከል 32 ዓይነት ዕፅዋቶች፣ 31 ብርቅዬና ድንቅዬ የዱር እንስሳትና ወደ ስድስት የሚጠጉ ዕፅዋት በብሔራዊ ፓርኩ ብቻ ሲገኙ በሌላው ዓለም ፈጽሞ አይገኙም፡፡ በባሌ ተራሮች ብሄራዊ ፓርክ ክልል ውስጥ ከሚገኙ 78 የሚደርሱ አጥቢ የዱር እንስሳት 17 የሚሆኑት በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ እንስሳት ናቸው፡፡

*የሐረና ደን›› ውስጥ ብቻ የምትገኘው የዝንጀሮ ዝርያ*

ከዚህ ባሻገር ለሳይንስና ኢኮሎጂ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው በደረታቸው የሚሳቡ ልዩ ልዩ እንስሳትና እንቁራሪቶችን ፓርኩ አቅፎ ይዟል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ለባህል መድኃኒትነት የሚውሉ 40 ከመቶ ዕፅዋቶችም ይገኙበታል፡፡ በእፅዋት እና በእንስሳት ብዝሃ ህይወት መበልፀግ ደረጃ ፓርኩ ከአለም 34ኛ ከአፍሪካ ደግሞ 12ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጧል፡፡ የባሌ ብሄራዊ ፓርክ በ “Bird lite International” በአለም ከሚገኙ አስፈላጊ የአዕዋፍ መኖሪያ ቦታዎች ጎራ ተመድቧል፡፡

በፓርኩ ከ280 በላይ የአዕዋፍ ዝርያዎች የሚኖሩ ሲሆን ሰባቱ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ናቸው፡፡ እንደ ዓለም አቀፍ የወፎች ድርጅት ሪፖርት ከሆነ የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ የአፍሪካ አራተኛው ‹‹በርዲንግ ሳይት›› ተብሎ ተመዝግቧል፡፡ በባሌ ብሄራዊ ፓርክ ዋቢ ሸበሌ፣ ዌብ፣ ዱማል፣ ያዶት እና ወልመል የተሰኙ ወንዞች ይፈሳሉ፡፡ በባሌ ብሄራዊ ፓርክ ከሚገኙ የዱር እንስሳት መካከል ቀይ ቀበሮ፣ኒያላ ፣ አጋዘን እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡

**የኢትዮጵያ ቀይ ቀበሮ**

ይህ ቀይ ቀበሮ አኗኗሩ በመንጋ ነው፡፡ አንድ መንጋ ከ3-13 አባላት ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ እያንዳንዱ መንጋ የራሱ የመኖሪያ አካባቢ ሲኖረው የአካባቢውን ድንበር ወንድ ቀይ ቀበሮዎች ያስከብራሉ፡፡ በርቢ ወቅት ሴት ቀይ ቀበሮ ከመንጋው አባላት ወንዶች ውጪ ግንኙነት ማድረግ አይፈቀድላትም፡፡ ከመንጋው አባላትም ጠንካራው ወንድ ከሴቶች ጋር ግንኙነት በማድረግ የተሻለ እድል አለው፡፡ የኢትዮጵያ ቀይ ቀበሮ ከማህበራዊ አኗኗራቸው ባሻገር በጠንካራ አዳኝነታቸው ጭምር ይታወቃሉ፡፡

ኒያላ /Mountain Nyalas/

ይህ የአጋዘን ዝርያ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ ብርቅዬ እንስሳ ነው፡፡ ቁመቱ 135 ሴ.ሜ በአማካኝ ይደርሳል፡፡ ሴቷ ኒያላ ከ150 — 200 ኪ.ግ ወንዱ ደግሞ ከ180–300 ኪ.ግ ይመዝናል፡፡ ኒያላ በባሌ ተራራማ አካባቢዎች ቁጥቋጦ፣ ሳር እና ዘርዘር ያለ የደን ሁኔታ በሚታይበት አካባቢ በስፋት ይኖራል፡፡ አንዲት ሴት ኒያላ ከ8-9 ወራት የሚቆይ የእርግዝና ጊዜ የሚኖራት ሲሆን በአንድ ጊዜ አንድ ትወልዳለች፡፡ ግልገል ኒያላ በመኖሪያ አካባቢው ብቻውን መንቀሳቀስ ከመጀመሩ በፊት ለ2 አመታት ያህል ከእናቱ አይነጠልም፡፡ ከዚህ በኋላ ሴቶች ወዲያውኑ የሚያረግዙ ሲሆን ወንዶቹ ወደ ላጤዎች ምድር ይቀላቀላሉ፡፡ ኒያላ ሳር፣ቅጠላ ቅጠል እና ቁጥቋጦ ይመገባል፡፡

የባሌ ብሄራዊ ፓርክ አስደናቂ የተራራ እይታዎች፣ ልዩ ስሜት የሚፈጥሩ ደኖች እና የውሃ አካላት ለቱሪስቶች ልዩ መስህብ ናቸው፡፡ በፓርኩ የሚገኙ የዱር እንስሳት እና አዕዋፍ ስብጥርም አስደናቂ ነው፡፡ ወደ ፓርኩ የሚጓዙ ቱሪስቶች የፓርኩን ተራራዎች በእግር በመውጣት /Trekking/ የማይረሳ ጊዜ ያሳልፋሉ፡፡ በፓርኩ የሚገኙ የዳንካ፣ ዌብ እና ሻያ ወንዞች እና ልዩ ልዩ የውሀ አካላት አሳ በማጥመድ ለሚዝናኑ ሀገር ጎብኝዎች የተለየ የእርካታ ምንጭ ናቸው፡፡ አሳ ለማጥመድ ግን ከፓርኩ አስተዳደር ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

